# በአንድ ፍላጻ ሶስት ጫፎች፡ ምስክርነት ከወንጀለኞች አንደበት?

## ክፍል ሁለት

(በህያዉ ቃል)

ከደርግ አገዛዝ ፍጻሜ ወዲህ የሥርዐቱን ገበና ዋና ትኩረታቸዉ ያደረጉ ቁጥር ያላቸዉ መጽሀፍት ታትመዉ ለገበያ ቀርበዋል ። ከነዚህም ጥቂቶቹ አንዳችም ጸጸት ባልታከለበት ጭካኔና ሽፍጥ በሚዳስሱት የታሪክ ዘመናት ታይተዉ የታለፉትን ኢ-ሰብአዊ ሁነቶች የሚያጠይቁ ናቸዉ ። በነዚህ ተርታ ከሚመደቡት አንዱ "ምስክርነት በባለስልጣናት አንደበት " በሚል ርዕስ በቅርቡ ለንባብ የበቃዉ ሲሆን በይዘቱ ከተካተቱት በርካታ የደርግ አገዛዝ ዘመን ክስተቶች መሃከል ከዚህ መጣጥፍ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸዉን (በሌሎች ስለመጽሃፉ በቀረቡ አስተያየቶች ያልተቃኙትን ) አንኳዋር አንኳዋሮቹን በማንሳት እንዳስሳቸዋለን።

"ምስክርነት " በደርጉ የምርመራ ባለሙያ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በግንቦት 2001 የታተመ ነዉ ። ማተሚያ ቤቱ ለደራሲዉ በስተቀር ባልታወቀ ምክንያት አልተመለከተም ። (ምናልባት ይህ ማተሚያ ቤቱን የመደበቅ ነገር ከወያኔ እስር ቤት፡ "ከወያኔ እይታ አምልጠዉ፡ " በጥራዝ የሚወጡ ጽሁፎች ሁሉ (የዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ ) አባዜ ይሆን ? ያሰኛል።) ታሪካዊ ይዞታ ላለዉ ለዚህ ድርሰት ዋናዉን አስተዋጽኦ ያበረከተዉ በደርጉ የአገዛዝ ዘመናት ጸሃፊዉ እንደ አንድ ግለሰብ በሥርዐቱ ዉስጥ የነበራቸዉ ተሳትፎና ቀረቤታ ነዉ። የዚያኑ ያህልም የደርግን መገርሰስ በተከተሉት ዓመታት ከቀድሞዎቹ አለቆቻቸዉ ጋር በእስራት ፡ ከዚያም በተከሰሱበት ወንጀል በተፈረደባቸዉ ቅጣት መሠረት በወህኒ ቤት ያሳለፉት ጊዜ በአያሌዉ አግዟቸዋል ።

ለሕትመት ዉጤቱ የተመረጠለት ርዕስ እጅጉን ማራኪና ለንባብ ግብዣ የሚጣራ ነዉ። በተለይም ጸሀፊዉ ሻምበል ለድርሰታቸዉ ማጠንጠኛ በሆነዉ የአገዛዝ ሥርዓት ዉስጥ በመንግስት ደረጃ በምስጢር በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ላይ የአዛዥ - ናዛዥ ሥልጣን በነበረዉ የደህንነት ሚኒስቴር በባለሙያነት የተሰማሩ ቀጭን የፖሊስ መኮንን የነበሩ፡ (እርሳቸዉም በድርሰታቸዉ ዉስጥ ዴጋግመዉ ይገበዙበታል) ከመሆኑ ጋር ተጣምሮ በአንባቢዉ ዘንድ የማወቅ ጉጉት በመጫር የናረ የንባብ ፍላጎት ያሳድራል ፡- ከሕዝብ የተሰወረ የመንግስት ምስጢርና እዉነት ተዘክዝኮ ይወጣል በሚል ግምት ።

ይህ ብቻም አይደል ። ሻምበሉ የሥራቸዉን ዉጤት መታሰቢያነት "በአብዮቱ ወቅት በዬትኛዉም ጎራ ተሰልፈዉ ሕይወታቸዉን ላሳለፉት ይሁንልኝ" ብለዉ ከጅምሩ መለፈፋቸዉ ሌላዉ የንባብ ማነሳሻ ሆኖአቸዋል ። መኮንኑን ተስፋዬ የዳር ታዛቢ ; ሌላዉ ቢቀር የተዛባዉን በቅጡ ለማስተካከል የተነሱ ቅን አገር ወዳድ ያስመስላቸዋል። ይህም የአገራችንን የቅርብ ታሪክ ለመጻፍ በተነሱ ወገኖች ዘንድ ተደጋግሞ የተስተዋለዉን ወደ አገለገሉት ሥርዓት በአድልዎ የመንጋደድ አባዜ ያስወግዳል የሚል ተስፋ በተደራስያኑ ልቦና ዉስጥ ለማሳደር አግዟቸዋል ።

ሻምበል ተስፋዬ ግና ይህን ሁሉ የተስፋ ካብ በመናድ የአንባቢያኑን ጥረት መና ለማስቀረት ብዙ ጊዜ አይፈጅባቸዉም። ወደ “መጽሐፋቸዉ“ ዐቢይ ይዘት ለመግባት ገና በጣት የሚቆጠሩ ገጾች ከመገላበጣቸዉ ከተሰጣቸዉ ግምት ያፈነግጣሉ። ታሪክ እጽፍ ብለዉ ያነሱት ብዕር ከዉሉ ተዛንፎ ቅዠት የወለደዉና ዉሃ የማያነሳ የመከላከያ ሃሳብ እያግተለተለ መደረት ይጀምራል። ጠቅለል ባለ ዕይታ፣ ሻምበል  ተስፋዬ ለታሪከኛዉ ድርሰታቸዉ ካሰመሩለት ግብ አንጻር በአንድ ተስፈንጣሪ ፍላጻ ሶስት ዒላማዎችን ለመምታት  ያለመ ቀስተኛ ይመስላሉ። በዚያችዉ በአንዲቱ የ”ምስክርነት“ ጥራዝ፣

አንድም፡- ለወደቀዉ ወታደራዊ አገዛዝ በታማኝነት ቆመዉ በተከላካይ ጥብቅና ለማገልገል፡

አንድም፡- አዲሶቹን አሳሪዎቻቸዉን በ”ጠላትህ ጠላቴ ነዉ “አገልግሎት ለማስደሰት፡

አንድም :-የገዛ ራሳቸዉን በዘመናት የደርግ አገልግሎታቸዉ (ያዉም በደህንነት ዘርፍ ) ከመጉደፍና ከመቀባባት ከማያመልጡበት የግፍ ግብረአበርነትና የደም እዳ አጣጥበዉ ለማሳዬት በተቻላቸዉ ሁሉ ይፍገመገማሉ ።

በእስራት ኮድኩዶ ወህኒ ያከረማቸዉን የወያኔን አገዛዝ (በፕሮፓጋንዳ ሥራ በማገዝ ) ለማስደሰት ያደረጉትን በሚመለከትማ ራሳቸዉም  የተነካካ ገበናቸዉን አልደበቁትም። በየዋህነት አይባል ነገር - የመርማሪዉን ሻምበል የአዕምሮ ብቃት (አይ-ኪዉ) ያለአግባብ ዝቅ ማድረግ ይሆንብናል። ይልቁኑ ለአሳሪዎቻቸዉ ያበረከቱትን አገልግሎት አክብዶ ለማሳዬት በሚመስል ሁኔታ በድርሰታቸዉ ያካተቱአቸዉን ዋቢ ማመሳከሪያዎች ለማሰባሰብ (ታሳሪዎቹን  ለመመረጅ?) በአደረጉት ጥረት የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ታሳሪዎቹ የደርግ ባለሥልጣናት “የወያኔ ሰላይ ነዉ“  በሚል ጥርጣሬ ሸሽተዋቸዉ እንደነበር በግልጽ አስፍረዉታል። በዚህ አድራጎታቸዉ ደርገኞቹ ሹማምንት በጊዜ ነቄ ማለታቸዉን እንገነዘባለን።  የወያኔን ሤራና ሰርጎገብ ተፈጥሮ ለመረዳት የሚያሻዉን የደመነፍስ ችሎታ ሥልጣን ሳይሆን እስራት ያሰላላቸዉ ይመስላል ።

ጸሓፊዉ ዋናዉ አነሳሳቸዉ ታሪክን ለትዉልድ መዝግቦ ለማስቀረት መሆኑን ምለዉ ይገዘቱበታል። ይሁን እንጂ ከ”ምስክርነት “መግቢያ  በፊት “ምስጋና “  በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር ባካተቱት የድርሰታቸዉ አካል ስለጽሁፋዊዉ ሥራቸዉ አወጣጠን የሚነግሩን እዉነት ስለ”ምስክርነት“  አጠቃላይ ይዘትና ጭብጥ ዐይነተኛ ማብራሪያ የሚሰጥ ነዉ ። በሮማዉያኑ ቁጥር : ገጽ 11 ላይ እንዲህ ይሉናል።------

“---በ1984 የትንሳዔ ዕለት ማታ ዶ/ር ዓለሙ አበበ : ሻለቃ ካሳዬ አራጋዉ :

ሻምበል ለገሠ አስፋዉና ጸሓፊዉ በካሣዬ ክፍል ቁጭ ብለዉ ሲያወሩ

ነበር። በጊዜዉ ጉዳዩን አንስተዉ ሲነጋገሩ ሁሉም ባለሥልጣናት ለሚቀ

ርቡላቸዉ ቃለመጠይቆች መልስ ሊሰጡ ፈቃደኝነታቸዉን ገለጹና ተስማ

ምተዉ ተለያዩ፡-----ወዲያዉ ሥራዉ በድፍረት ተጀመረ ።"

የዚህን የእስር ቤት "ስብሰባ " ተካፋዮች (ዋናዎቹን የቀይ- ሽብር መሐንዲሶች-ዓለሙንና ለገሠን ያቀፈ ) በማንጸር የሻምበል ተስፋዬን የሥራ ድርሻ ከግል የሥነ-ጽሁፍ "ችሎታ "ጋር የተያያዘ ብቻ አድርገን እናቅልለዉ ብንል እንኳዋ ፡ የትንሳዔ ማታዉ "ወሬ " ከተራ "ወሬነት " የተላለፈ ግብ የነበረዉ ; ታሪክን በግልባጩ "አስተካክሎ " የማቅረብ ተልዕኮ የነበረዉ መሆኑን የሚያመላክት መሆኑ አይቀርም። "ጽንሱ ያላማረ በልደቱ ይስተካከላል፡" ካልተባለ በቀር "መጽሓፉ " ከዉጥኑ አንስቶ አንዳች ተልዕኮ የተሰጠዉ ለመሆኑ በይፋ የሚያስረዳ ነቃሽ ነዉ። በደምሳሳዉ የሻምበሉ ድርሰት ጽንሱ በ"እስር ክፍል፡" ምስክርነቱ በወንጀለኞች. የነበረዉን ያህል ተልዕኮዉም ሆነ ግቡ ኢትዮጵያንና ትዉልድን አጣምረዉ የገደሉ እፍረተቢስ ጭራቆችን ከደም ዕዳ ተጠያቂነት ማስመለጥ ነዉ ማለቱ የደፋር ማጠቃለያ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም ።

– ይቀጥላል -